የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ህዳር ፭ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.7
ADDIS ABABA 15th November, 2004


## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፪/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.**


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በታላቋ ሕዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥት መካከል በባህል፣ በወጣቶችና በስፖርት መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ.... ገጽ. ፪ሺ፱፻፴፫


## CONTENTS

**Proclamation No. 422/2004**


Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya on Cooperation in the Field of Culture, Youth and Sports Proclamation. ... Page 2933


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፪/፲፱፻፺፯

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በታላቋ ሕዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥት መካከል በባህል፣ በወጣቶችና በስፖርት መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በታላቋ ሕዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ወዳጅነትና ትብብርን ለማስፋፋት የሚያስችሉ መሠረታዊ ስምምነቶችን ከታላቋ ህዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥት ጋር የፈረመ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀደም ሲል ባደረገው ስብሰባ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በታላቋ ህዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥት መካከል በባህል፣ በወጣቶችና በስፖርት መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወሰነ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 422/2004.

### A PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GREAT SOCIALIST PEOPLES LIBYAN ARAB JAMAHIRIYA ON COOPERATION IN THE FIELD OF CULTURE, YOUTH AND SPORTS.

**WHEREAS,** the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has entered in to basic Agreement with the Great Socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya for the promotion of friendly relations and cooperation among the people of the two countries.

**WHEREAS,** the House of People's Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya on Cooperation in the Field of Culture, Youth and Sports signed on 27, January 2004.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is here by proclaimed as follows.


ያንዱ ዋጋ Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በታላቋ ሕዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥት መካከል በባህል፣ በወጣቶችና በስፖርት መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፪/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱን ስለማፅደቅ</u>**

ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በታላቋ ህዝባዊ ሶሻሊስት ሊቢያ አረብ ጀማህሪያ መንግሥትና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በባህል፣ በወጣቶችና በስፖርት መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በዚህ አዋጅ አፅድቋል።

**፫. <u>አዋጁን የማስፈፀም ሥልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከህዳር ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ህዳር ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya on Cooperation in the field of Culture, Youth and Sports Proclamation No. 422/2004."

**2. Ratification of the Agreement**

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Great Socialist Peoples Libyan Arab Jamahiriya on Cooperation in the field of Culture, Youth and Sports signed on 27, January 2004, is here by ratified by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**3. Power of Implementation**

The Ministry of Youth, Sports and Culture of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall have the power to implement this Proclamation

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come enter into force as of the 15th date of November,2004.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of November, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**